# ትዝታ ስለ ጋምቤላው ዘመቻ

*በገዛኸኝ ዓለሙ*

## *አሁንስ የት ይሆን?*

***<u>እንደመግቢያ</u>***

*ጊዜው እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጥር የ1977 ዓመተ ምህረት ወርኃ ክረምት ነው። በጋምቤላ ሰማይ ስር በጊሎ አቦል የመልሶ ማቋቋም ዘመቻ ጣቢያ እንገኛለን። ይህ የዘመቻ ስራ በመንግስት የታወጀ ሲሆን በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች በድርቅ የተጎዱ ወገኖችን ወደ ሌሎች በቂ ዝናብ የሚያገኙ አካባቢዎች በማጓጓዝና በማስፈር ራሳቸውን በእርሻ ስራ እንዲችሉ ለማድረግ የታቀደ የቅድመ ዝግጅት ሥራ ነው።*

*የጊሎ አቦል ዘመቻ (ሰፈራ) ጣቢያ ኃላፊ ቆፍጣናው፣ ባለብዙ ታሪክና አዛውንቱ ዶ/ር በየነ ጭጬ አይበሉ ናቸው። ዘማቾቹም ከዓለምማያና ከደብረ ዘይት ኮሌጆች ተመድበን የመጣን ትጉኅን ነን። ወቅቱ ክረምት ቢሆንም የጋምቤላ ሙቀት የክረምት አይመስልም። ዝናቡም ሲወርድ ሰማዩ በሙሉ ኃይሉ የተከፈተ ነው የሚመስለው። የአፈሩ ነገር ደግሞ ያስገርማል። በደረቁ ወቅት እንኳን በዶማና በገሶ፣ በዲጂኖም ቢሆን የምሰሶ ማቆሚያ ጉድጓድ ለመቆፈር በጅ የማይለው ኮትቻ አፈር ዝናቡ ዘንቦ ሲያባራ ለመራመድም የሚያስቸግር ማጥ ይሆናል።*

*በዚህ የዘመቻ ጣቢያ በቆየንባቸው ወደ ሦስት ወር የሚጠጋ ጊዜ ብዙ አስገራሚ፣ አሳዛኝ፣ አስቂኝ ወዘተ ክስተቶች ተስተናግደዋል። ፈገግ ካሰኙን ክስተቶች የሚከተለውን ላስታውሳችሁ። በቦታው ላልነበራችሁም እንዲህ ላውጋችሁ።*

*<u>አሁንስ የት ይሆን?</u>*

*የምሳ ሰዓት ደርሶ ዘማቹ ከየአቅጣጫው ምሳ ወደ ሚዘጋጅበት ሰቀላ መጥቶ ድርሻውን ለመቀበል በሁለት ረድፍ ተሰልፏል። እያንዳንዱ ዘማች የሚመጣውም ባዶ እጁን ሳይሆን በነፍስ ወከፍ የታደለውን አነስተኛ ሳህን፣ ሹካና ማንኪያ ይዞ ነው። ታዲያ እነዚህ የመመገቢያ ዕቃዎች ሁልጊዜም በጥንቃቄ ታጥበውና ተወልውለው የሚያዙ ናቸው። አለያ በጥቂት ቸልተኝነት ላልታሰበ ኮመን ኮርስ ያጋልጣሉ። ዘማቹም በተለያዩ አጋጣሚዎች ከደረሰበት ሁኔታ በመነሳት የመመገቢያ ዕቃዎችን በጥንቃቄ መያዙ ግዴታው ሆኗል። ጓደኛችን ከድሮ እንደሚለው ''ከውሃ የቀጠነ፣ ከጄት የፈጠነ….'' ዱብዳን ለማምለጥ አንዱ ጥንቃቄ ይህ ነበር። የጋምቤላው ደግሞ የተለየ ነውና።*

*ከሰልፉ ርዝመት በተጨማሪ የጸሐዩ ግለት፣ ንፋስ የለሹ ወበቅ፣ በግንባር፣ በጀርባ ወዘተ የሚንቆረቆረው ላብ፣ መቼ ድርጎዬን ተቀብዬ ወደ መጠለያዬ በሔድኩ ያሰኛል። ከምሳ በኋላ በመጠለያ ዳሶች ለአጭር ሰዓትም ቢሆን የሚኖረው የእርስ በርስ ተረብ፣ ብሽሽቅና አልፎ አልፎም ትንሽ እንቅልፍ ትናፍቃለች። በዚህ የሰልፍ ሒደት ነው እንግዲህ ከሰልፉ አንድ አቅጣጫ የምሳ ሳህንን በማንኪያ በመምታት ኳ ኳ ኳ የሚል ድምጽ መሰማት የጀመረው። ምክንያቱ ባይታወቅም የተጀመረው የኳ ኳ ቴ ድምጽ የተሰለፈው ዘማች ተቀባበለው። ድምፁም እየጎላ፣ እየደመቀ፣ ቅርጽ እየያዘ መጣ። የሙዚቃ ስርዓት የያዘ ኳ ኳ ኳ ኳ ኳ ኳ…..። ቀጥሎ በውል ካልተለየ አቅጣጫ ጎርነን ያለ ድምጽ በሙዚቃ ቃና ''እቴ እይላቸው የት ነው? '' ሲል ዘለግ አድርጎ ጠየቀ። በሚገርም ሁኔታ ከሌላው አቅጣጫ ''እዚያው ጀርመን ነው! '' ሲል በተመሳሳይ ዜማ ምላሽ ሰጠ። ከዚያ በኋላማ ምን ይነገራል። ጠያቂዎች በርከት ብለው፣ መላሾችም በብዙ መቶ ሆነው፣*

### *እቴ እይላቸው የት ነው?*

## *እዚያው ጀርመን ነው!*

*እያለ በሳህንና ሹካ ታጅቦ ህብረ ዜማው ቀለጠ። የጊሎ አቦል ሜዳ በጎርናና ድምጾች ውብ ዜማ ተስረቀረቀ። በፀጥታ የሚፈሰው የጊሎ ወንዝም ህብረ ዜማውን የተቀላቀለ መሰለ። በርቀት የነበረ ዘማችም ምን ተፈጠረ ብሎ ....*

*እይላቸው ዘውዴ የሦስተኛ ዲግሪ ትምህርቱን ለመከታተል በጀርመን ሀገር የሚገኝ የኮሌጁ ባልደረባና መምህር ነው። ለምርምር ስራው ወደ ኮሌጁ በመጣ ወቅትም Introduction to Soils  የሚል ኮርስ አስተምሮናል። እይላቸው ቁመቱ ዘለግ ያለ፣ መልከ መልካም፣ አረማመዱ ያማረ፣ ደርባባ፣ በግምት ሰላሳዎቹ አጋማሽ ላይ የደረሰ ጎልማሳ የሚባል ዓይነት ነው።*

*እይላቸው ሲያስተምር የሚጠራቸው የአፈር የኬሚካል ይዘት ስሞች ብዛትና ቀመር ሁሌም እንግዳ ይሆኑብናል። Dolomite, Kaolinite, Montmorillonite ..... እያለ በብዛት የማናውቃቸውን ባዕድ ስሞችና ቃላት ሲደረድር የእንግሊዘኛ ቃላት መሆናቸውን እንጠራጠራለን። አንዳንዶቻችንም ይህ ሰውዬ እንግሊዘኛው ሲጠፋበት ጀርመንኛ እየቀላቀለ ሳይሆን አይቀርም ብለን ማማታችን አልቀረም።*

*የስላቅ ሕብረዝማሬው በሳህን፣ ሹካና ማንኪያ ሙዚቃ ታጅቦ እንደቀጠለ፣ እንደደመቀ ነው። ምናልባትም ደቂቃዎች ተቆጥረዋል። በሕብረዝማሬው ሁሉም ደስተኛ ይመስላል። ጮክ ብሎ ያስነካዋል፣ እስክስታም የሚቃጣው አልጠፋም።*

## *እቴ እይላቸው የት ነው?*

## *እዚያው ጀርመን ነው!* *እየተባለ ነው!*

*በዚህ መሐል ወደ ሰልፉ ተራዋን ጠብቃ ለመቀላቀል ከጓደኞቿ ጋር እየመጣች የነበረች አንዲት ቀላ አጠር ያለች ዕንስት ድንገት እንደደነገጠ፣ እንደበረገገ ሰው ከጓደኞቿ ተነጥላ ወደ መጣችበት አቅጣጫ ስትሮጥ ታየች ~ ወደ ኋላም አልተመለከተች። ጓደኞችዋንም አልጠበቀች። በሚገርም ሁኔታ የሷ ድንጋጤ የተጋባበት ይመስል ሕብረዝማሬው መደነቃቀፍ፣ በሳቅና ሁካታ መተካት ጀመረ። የዕንስቷ ጓደኞች ይከተሏት አይከተሏት ግልጽ አልነበረም።*

*እንደ ድንገት በግብታዊነት ተጀምሮ እያማረና እየደመቀ የመጣው፣ የተጠና እስኪመስል ድረስ አምሮ የነበረው ሕብረ ዝማሬ አጨራረሱ አላማረም። ድምፀቱ ሁሉ እያነሰና እየቀነሰ ሔደ። ዕንስቷ ከአይን ስትርቅ ዝማሬውም፣ የሳህንና ማንኪያ ኳኳቴውም እየኮሰመነ ሔደ። ሰልፈኛውም በክስተቱ በመሳሳቅ፣ በቡድን እየሆነ ከማውራት አልፎ ሀሳቡን ወደ መጣበት ጉዳይ መመለስ ጀመረ።*

*<u>እንደ ማጠቃለያ</u>*

*መቼም በዚህ ዕለት እንደነገሩ በተሰራው የምግብ ማብሰያ ሰፊ ዳስ ውስጥ በዚያ ወበቅና ንዳድ፣ የማገዶው ወላፈን እየገረፋቸው፣ ጭሱ እያጨናበሳቸው ምግባችንን የሚያበስሉት ቀጥሎም የሰሩትን ምግብ በየሳህናችን ላይ የሚጨልፉልን የምግብ ቤቱ ሰራተኞች ሁሉ በትዕይንቱ ሳይዝናኑ የቀሩ አይመስለኝም። ተመጋቢውም እንደሌላው ጊዜ አንሿል ጨምር፣ አሯል ቀይር ብሎ ሳይሟገት ድርሻውን ይዞ ወደ መመገቢያ ስፍራው (መጠለያው) የተፈተለከ ይመስለኛል። ይህን የሚያዝናና ድባብ ማን ማበላሸት ይፈልጋል!*

*ትዕይንቱ ግን በዚህ አላበቃም። እንደኔ ዓይነቱ ድምፀ ሰላላም ማገር ሲቆርጥ፣ ሀረግ ሲመዝ፣ ቋሚ ሲሸከም ... ''እቴ እይላቸው የት ነው?'' እያለ በለሆሳስ እያንጎራጎረ ውሎ አመሸ። ለቀናትም ቀጠለ።*

*አሁንስ ፕሮፌሰር / ዶ/ር እይላቸው የት ይሆን? መቼም በሰባዎቹ አጋማሽ ያለ አዛውንት፣ አንቱ የተባለ የአፈር ሳይንቲስት፣ የሀገር ዋርካ፣ መራቂ፣ አስታራቂ ይሆናል ብዬ አስባለሁ። እሱ ባያውቀውም ይህን የመሰለ ከአራት ዓስርት ዓመታት በኋላ የሚተረክ ትዝታ ስላተረፈልን ረዥም ዕድሜ፣ ጤናና ሰላም ከመልካም ፍቅር ጋር ተመኘሁለት።*

*ውድ ዓለምማያዎቼ እኔ ትዝታዬን እንዲህ አሰፈርኩ። እናንተ ደግሞ የጎደለውን ሞልታችሁ የዘመመውን አቅንታችሁ ለብርሃን አብቁት ። መልካም የአርባኛ ዓመት ክብረ በዓልም ተመኘሁ!!!!!! ገዛኸኝ ዓለሙ ታደሰ*